# በኤርትራ "የሊጥ ገበያ ደርቷል" ተባለ

ከሰላሳ ዓመታት የእርስ በርስ ጦርነት በኂላ፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ኪሳራ (With the expense of Ethiopia) ከእናት ሀገሯ ተገንጥላ የራሷ መንግስት ያቋቋመችው የኤርትራ ሕዝብ ሊቋቋመው በማይችለው የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ መውደቁን የአካባቢውን መረጃዎች አሰባስቦ ዘገባ የላከልን ሪፖርተር አስታወቀ፡፡

"ኤርትራ፤ እ.ኤ.አ በ1891 ዓ.ም በቅኝ ገዥው የጣሊያን ፋሽስት መንግስት አገዛዝ ቀንበር ሥር ከወደቀችበት ጊዜ ጀምሮ በቅኝ አገዛዝ፣ በሞግዚት አስተዳደር፣ በፊውዳልና በወታደራዊ አስተዳደር ምክንያት አንጻራዊ ሰላም አግኝቶ የማያውቀው የኤርትራ ሕዝብ፤ አገር የመመስረት ዕድል ቢያገኝም ዛሬም በአምባገነናዊ የአፈና ሥርዓት ውስጥ ሆኖ በመማቀቅ ላይ መሆኑን መረጃዎች ያስረዳሉ" ሲል የዜና ምንጩ ዘግቧል፡፡

የዛሬ 18 ዓመት ከደርግ አምባገነን ወታደራዊ አስተዳደር ተላቃ ወደ ሌላ የለየለት "ጨቋኝ" ሥርዓት የተሸጋገረችው ኤርትራ፤ "ሕገ መንግስት የሌላት፣ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ተካሂዶባት የማያውቅ፣ ነፃ ፕሬስ የማይታይባት፣ ለመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ያልታደለች፣ በአንድ ፓርቲና በአንድ አምባገነን ግለሰብ ቁጥጥር ሥር ሆና ሕዝቧ በስደት፣ በርሃብና በድንቁርና ጨለማ ውስጥ መከራውን እያየ ነው" ሲል የዜና ምንጩ ጨምሮ ገልጿል፡፡

በኤርትራ ሕዝብ ላይ የተጫነው አምባገነን ሥርዓት በሕዝቡ ላይ የሚያወርደው መከራ አልበቃ ብሎት ከጎረቤት ሀገሮች ጋር በሚፈጥረው አምበጓሮና ጦርነት ምክንያት ሁሉም ኤርትራዊ "ወታደር ሆኗል" የሚባልበት ደረጃ ላይ ደርሷል ይላል የዜና ምንጩ ዘገባ፡፡

በጦርነትና በጠብ ጫሪነት ታዋቂ መሆንን የመረጠው የኤርትራ መንግስት ከጎረቤቶቹ ጋር ከመጋጨት አልፎ በተለያዩ ሀገሮ ያሉ "ዓለም አቀፍ አሸባሪዎችን" የሚያደራጅና የሚረዳ በመሆኑ፣ በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ያለው ተቀባይነት "መና ቀርቷል" ይላል የዜና ምንጩ፡፡ አክሎም፤ "በዚሁም ምክንያት ኤርትራ ከኢጋድ አባልነት ተወግዳለች፡፡ በአፍሪካ ሕብረት ተወግዛለች፡፡ በቅርቡ ደግሞ በተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት በኩል ማዕቀብ ተጥሎባታል" በማለት የዜና ምንጩ ዘገባ በዝርዝር ያስረዳል፡፡

ብዙሃኑ የኤርትራ ሕዝብ ጊዜውን በወታደራዊ ስልጠና ስለሚያሳልፍ፣ በተለይም በግብርና ሥራ ላይ የተሰማራው ዜጋ ቁጥር አነስተኛ መሆኑና ለምግብ የሚሆን እህል ከጎረቤት አገሮች ለመሸመትም ባለመቻሉ ሕዝቡ ተማሯል፡፡ በጥቂት የኤርትራ አርሶ አደሮች የተገኘው ምርትም ቢሆን ገና ከማሳው ላይ ሳይነሳ መንግስት በተመነው ዋጋ ለመንግስት እንዲሸጥ ስለሚደረግ ሸማቹ ህብረተሰብ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ገብቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ማናኛውም ሰው ምንም ዓይነት የእህል ምርትም ሆነ ዱቄት ገበያ ላይ አውጥቶ መሸጥ ስለተከለከለ፣ በአሁኑ ወቅት ኤርትራ ውስጥ የተቦካ ሊጥ መግዛትና መሸጥ የዕለት ከዕለት ትዕይንት መሆኑን የዜና ምንጩ ዘገባ ያስረዳል፡፡

"የተሻለ የአስተዳደር ሥርዓት እናገኛለን፡፡ ከአምባገነኖች አስተዳደር እንላቀቃለን" ብለው ከኢትዮጵያ የተገነጠሉት ኤርትራውያን "አባቶቻችን 'አንዲት ኢትዮጵያ ወይም ሞት' ያሉት ትክክል ነው፡፡ እማማ ኢትዮጵያ ማሪን" የሚሉበት አስመራሪ ወቅት ላይ ደርሰዋል ሲል የመረጃ ምንጫችን ዘገባ አመልክቷል፡፡